# አድዋ

ቴዎድሮስ ተወልዶ ህልም ባያልም
ምኒልክ ተነስቶ በማለዳ ጥሃይ ያን ባይተረጉም:
የኢትዮጵያ ጀግና ትርጉሙን አዳምጦ ባይተባበር:
የሰላቶ መንጋ ድንግል አገራችን ያረክሳት ነበር:

የአድዋን ድል ስናስብ የአያቶቻችን ተጋድሎ እና ጀግንነት ከምንገምተውና ከምናሰበው በላይ መሆኑን ለመረዳት ይከብዳል ብየ አስባለሁ:: በአምስት የወታደራዊ ሙያተኛ ጀኔራሎች በበርካታ ኮሎኒሎችና ባለሌላ ማዕረግ መኮንኖች የተመራን እና በመሳሪያ ጥራትም ሆነ በስንቅና ትጥቅ ዝግጅት ከአያቶቻችን በብዙ እጅ የላቀና የተደራጅን ጦር በስዓታት ብቻ በሚቆጠር ውጊያ ብትንትናውን አውጥቶ ድል መቀዳጀት እጅግ በጣም አስደማሚ ነው::እንደ ዚህ አይነት ወሳኝ የሆነና በአጭር ጊዜ የተጠናቀቀ የጦርነት ድል በዓለም የመጀመሪያው እንደሚሆን አልጠራጠርም::

ይህን የመሰለ ወሳኝ ድል ለመቀዳጀት የተዋጊው ወኔና ጀግንነት ብቻ ሳይሆን የአመራር ስልት ብስለትና ብቃትንም ይጠይቃል::አጤ ምኒልክ የአሳዩት የአመራር ስልት እና ብቃት:ተወዳጅ ንግስታቸው እቴጌ ጣይቱ ካሳዩት ድፍረትና መላ ጋር በመቀናጀቱ ኢትዮጵያ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ቀንበር ሳይጫንባት በነፃነቷ ለመቀጠል ችላለች:: ስለዚህም ነው ያ ስሙ የማይታወቅው ገጣሚ

ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ:
ግብሩ እንቁላል ነበር ይኸን ጊዜ አበሻ:

ሲል ስንኙን የቋጠረ::
ምኒልክንም ሆነ ያን የእሳቸውን ትውልድ የምንወድና የሚገባቸውን ክብር የምንለግስላቸው ብቻ ሳንሆን የሚጠሏቸውም ቢሆኑ የተጋድሏቸው ውጤት በሆነው ነፃ አገርና ሕዝብ ሁነን በመቀጠላችን ይኩራራሉ:: ይሁን እንጂ የተወሰኑ የባንዳ ልጆችና የልጅልጆች ለምኒልክ ካላቸው ስር የሰደደ ጥላቻ የተነሳ በፈጠራ ድርሰት ስማቸውን ጥላት ሲቀቡ እየተመለከትን ነው:: እንደ ምሳሌ የሸራሮው የታሪክ ምሁር ነኝ ባይ ገብረ ኪዳን ደስታ የሚባልን ግለሰብ ብንወስድ የአድዋ ድል የምኒልክ ሳይሆን የእራስ መንገሻና የራስ አሉላ ድል ነው እያለ በመጽሐፍም በመገናኛ ብዙሃን በሚያደርገው ቃለመጠይቅም ከእውነት ጋር የማይገናኝ የፈጠራ ትርከት ለወጣቱ ትውልድ እያስተማረ ይገኛል:: ታሪካዊ ሃቁ ግን የሚመሰክረው ግን ተቃራኒውን ነው:: እራስ መንገሻ በአንድ ጄኔር ኮሎኔል ከሚመራ  አንድ  ሻለቃ ጦር ጋር ሦስት ጊዜ ተዋግተው ሦስቱንም ጊዜ ድል ሆነው ጠቅላላ ትግራይ በጣሊያ ቁጥትር ስር ወድቃ መንገሻም በምኒልክ ጥያቄ ወሎ ከእራስ ሚካኤል ተጠግተው የሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ዘማች እስቲደርስ ድረስ እንደ ከረሙ የአደባባይ ሀቅ ነው:: ያ  ባይሆንማ ኑሮ አምባላጌም ሆነ መቀሌ ላይ ጦርነት ባልተደረገ ነበር:: ገብረ ኪዳን ደስታ እና መሰሎቹ በተለይም የ1960ዎቹ ጥራዝ ነጠቅ አብዮተኞችና የነገድ ቸርቻሪዎች ምኒልክንና በእየ እርከኑ የነበሩትን መሪዎች ፊውዳል ትምክህተኛ ነፍጠኛ በሚል የኮድ ስም ለአገር የከፈሉትን መስዋዕትነት ባለማሰብ በውሸት እንደ ክፉ ሰሪ ይወነጅሏቸዋል::

እውነቱ ሲገለጥ ግን እነዚያ በውሸት የሚወነጀሉት አባቶቻችን በአጥንትና በደማቸው ነፃነቷንና አንድነቷን ጠብቀው ያስረከቡነን አገር ወደ አለመኖር ገፍተው በመጣል ሊበታትኗት ከጫፍ ያደረሷት እነዚህ የምኒልክን እና የጦር አበጋዞቻቸውን ስም በፈጠራ ታሪክ የሚያጠፉት አብዮተኞች ነን ባዮች ናቸው:: ፊውዳል ተብለው የሚወገዙት ኢትዮጵያውያን ግን ለህይወታቸው ሳይሳሱ በየጦር ግንባሩ ከወንድሞቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር እየወደቁ ነው የምንኮራባትን ነፃ አገር ያስረከቡን:: የአድዋ ድል እውን የሆነው ስማቸው በታሪክ ማህደር ባልተመዘገበላቸውና ባልተዘመረላቸው ጀግኖቻችን ህይወታቸውን ስለገበሩ ነው::ከአንድ ቤት ሦስት አራት ወንድማማቾች ዘምተው አንድ ሁለት በህይወት ሲመለስ ሌላው እየተሰዋ ነው ነፃነታችን ተጠብቆ የኖረው:: እንደ ምሳሌ ስማቸው በታሪክ ማህደር ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል እራስ ሙሉ ጌታ ይገዙን ብንወስድ በወጣትነታቸው አድዋ ዘምተዋል::  ከአርባ ዓመት በሁዋላ ጣሊያን እንደገና ስትወረን እድሜአቸው ከሰማኒያ ዓመት በላይ የነበሩ አዛውንት ቢሆኑም በዚህ የሽምግልናቸ  ዘመናቸው ዘምተው ሲዋጉ እና ሲያዋጉ አስራት እና ታደሰ ሙሉ ጌታ ከሚባሉ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ለአገራቸው ተሰውተዋል:: በዚህም ቤታቸው ተዘጋ ማለት ነው:: የኢትዮጵያ የፊውዳል ታሪክ ማለት ይህ ነው:: የመስዋዕትነትና አመራር በምሳሌ::

ሌላው በታሪ ማህደር ስማቸው ከተጠቀሱት አዋጊዎች መካከል ፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ ናቸው:: እኒህ ድንቅ ኢትዮጵያዊ በሰላም ጊዜ ዲፕሎማት በመሆን የዲፕሎማቲክ ልኡክ መርተው ወድ ሞስኮ እንዲሄዱ በአጤ ምኒልክ ታዝዘው የተላኩበትን ተግባር በብቃት ፈጽመው እንደተመለሱ የአደዋ የክተት አዋጅ ታወጀ:: ፊታውራሪ ዳምጠውም የዲፕሎማት ባርኔጣቸውን አውልቀው የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ጎራዴና ጋሻቸውን አንስተው ወደ ጦር ግንባር ዘመቱ:: ለአገራቸው በነፃነት መቀጠል ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር ለተተኪው ትውልድ ኩራት በወኔና ጀግንነት ሲዋጉና ሲአዋጉ እጅግ ውድ የሆነውን ዋጋ ከፈሉ:: አደዋ ላይ ተሰው:: ልጅ የአባቱን ጋሻ ያነሳል የሚባለውን ብሂላችን የሚገልጽ ሁኔታ በዚህ ቤተሰብ ላይ ተከስቷል:: ከአርባ ዓመት በሁዋላ የአድዋን ቂም ለመበቀል ጣሊያን እንደ ገና ኢትዮጵያን ስትወር በሱማሌ በኩል የከፈተችብንን ወረራ ለመመከት የተሰለፈውን የኢትዮጵያ ጦር ከሚመሩት መካከል አንደኛው አድዋላይ የተሰውት ጀግና የፊታውራሪ ዳምጠው ከተማ ልጅ እራስ ደስታ ዳምጠው ነበሩ:: እራስ ደስታም እንደ አባታቸው ከወራሪ ጠላት ጋር ሲፋለሙ የአባታቸው ጽዋ ደረሳቸውና ኦጋዴን ላይ ተሰው:: ከ39 ዓመት በሁዋላ በ1967 ዓም የፊታውራሪ ዳምጠውን የልጅ ልጅ የእራ ደስታን ልጅ እስክንድር ደስታን ኢትዮጵያውያን ነን በሚሉ ጉግማንጉግ መሪዎች ወይንም አብዮተኞችን ነን ባዮች ያለፍርድ ተረሸነ::

እኛ ኢትዮጵያውያኖች ውለታ ስንከፍል እንዲህ ነን:: የውለታ መክፈል ነገር ሳነሳ በደጃዝማች በላይ ዘለቀ ላይ የተፈጸመው ግፍ ትዝ አለኝ:: ደጃዝማች በላይ ዘለቀ በታሪክ እንደሚታወቁት በአምስት ዓመቱ የጣሊያን ወረራ ጊዜ ለአገራቸው ልዋልዓዊነት ለሰንደቅ ዓላማቸው በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ እንደገና እንድትውለበለብ ዱር ቤቴ ብለው ከጠላት ጋር በመፋለም ለወራሪው ጠላት የእግር እሾህ ሁነው መንቀሳቀሻ የነሱ ጀግና ነበሩ:: በዚህ የነፃነት ትግላቸው ወቅትም ወንድማቸውን እጅጉ ዘለቀን ግብረዋል:: ይሁን እንጅ በእርሳቸው እና መሰሎቻቸው ትግል ልዋላዓላዊነታችን ከተመለሰና ሰንደቅ ዓላማችንም እንደገና ከፍብላ ከተውለበለበች በሁዋላ እንደ ተራ ሌባ በአስራ አምሥት ሳንቲም ገመድ ተሰቅለው ተገደሉ:: የሚገርመው ነገር ደግሞ በላይ ዘለቀ በገመድ ተንጠልጥለው እንዲገደሉ ፍርዱን ከገመደሉት ሰዎች ውስጥ ኢትዮጵያ በጠላት ተወራ ሳል አገር ለቀው ተሰደው ውጭ አግር የነበሩ ሰዎች መኖራቸው ነው::አባኮስትር በላይ በስቅላት እንዲሞቱ ተፈርዶባቸው ከችሎት ሲወጡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲያዩ የተናገሩት "አንቺ ሰንደቅ ዓላማ ለአምስት ዓመት ማተቤ ነበርሽ ዛሬ ለዚህ አበቃሽኝ:: አንች አገሬ አንች ኢትዮጵያ በድየሽም ተሆነ ነብሴን አትቀበላት ካልበደልሁሽ ደግሞ ወንድ አይብቀልብሽ::" ይህ የቅን ሰው እርግማን ደርሶብን ይህው አገራችን ወንድ አልበቅልባት ብሎ በማንም የባንዳ ልጆችና የልጅልጆች በመጥፋት ላይ ትገኛለች::

ምኒልክን እነ ገብረ ኪዳን እና ከዚያ አካባቢ በበቀሉና በልቦለድ የታሪክ ድርሳን ላይ የተሰማሩት ብቻ አይደሉም በሃሰት የሚወነጅሏቸው:: በኦነግ ርዕዮትዓለም የተጠመቁ የኦረሞ ጽንፈኞችም ያለሰማቸው ስም ያለተግባራቸው ተግባር እየሰጡ ይከሷቸዋል::ምኒልክ ጡት ቆረጠ ብለውም ሃውልት ሰርተው ትውልድን የተሳሳተ ትምህርት በማስተማር ላይ ናቸው:: ነገር ግን ይህ አይነት ክስ ማስረጃ የለውም የእሴት ጡት መቁረጥ ባህላችንም አይደለም:: ይልቁንስ የሰውን አካል መቁረጥ በተለይ ደግሞ የወንድን ብልት መቁረጥ ማን እንደሚያደርገው የታሪክ ድርሳናትን ቢያገላብጡ የማን ባህል መሆኑን ያገኙት ነበር::

ያ ስሙ የማይታወቀው ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻን ግጥም የፃፈው ሰው ከዚያው ግጥም ውስጥ አንዷት እንደ ትንቢት ተናጋሪ የቋጠራት እንዲህ የምትነበብ ስንኝ አለች::

ምኒልክ ተጉዞ የምትጠይቀኝ:
ፊትም አላለፈ ከሁዋላም አይገኝ:

ፊትም አላለፈ የሚለው አከራካሪ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም ከአጤ ምኒልክ በፊት በርካታ ታላላቅ ነገሥታት ኢትዮጵያን መርተዋል::እንደ ጦረኛው እምደ ጺዮን እንደ ቅዱሱ ላሊበላ በዓለም ላይ አስደናቂ የሆነውንና ከምንኮራባቸው ቅርሶች መካከል የሆኑትን የላሊበላን አቢያተ ክርስትያናት ያነጸ:: እንደ ቀዳማዊ ዮሐንስ (በጎንደር ፃዲቁ በመባል የሚታወቁት) ከሰው ልጆች አልፈው የእንስሳትን መብት ያስከበሩ ነገሥታት አልፈዋል:: ከሁዋላም አይገኝ ያለው ትንቢት ግን ደርሶብን ከምኒልክ በሁዋላ እንደ ምኒልክ ያለ መሪ ኢትዮጵያ አላገኘችም::
ምኒልክ ታጋሽ ትሁትና ለጥፋተኞች ምህረት የሚያደርጉ በሰው ልጆች እኩልነት የሚያምኑ መሪ ነበሩ:: ለምሳሌ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት እና ከንጉሥ ጦና ጋር በተለያየ ጊዜና ቦታ ጦርነት ገጥመው ሁለቱንም ድል አድርገና በጦርነቱ አቁስለው ማርከዋቸዋል::ምኒልክም መቁሰላቸውን ሲያዩ አዝነው ደማቸውን ፋሻ አምጡልኝ ብለው በፋሻ በእጃቸው

ጠርገው እንደ ምርኮኛ ሳይሆን ወንድሙ እንደቆሰለበት ተንከባክበው አድነው ወደ ግዛታቸው መለሷቸው::ከዚያ በሁዋላ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር እንደሚዋደዱ ወንድማማች እንጂ እንደ ስልጣ ተወዳዳሪ ሳይተያዩ እየተመካከሩ ሲመሩ ኑሩ:: እራስ ጎበና ዳጬ ለምኒልክ ታማኝ ባለሚልና ቀኝ እጅ ነበሩ:: ምኒልክም ለጎበና ላቅ ያለ ፍቅር ስለነበራቸው መጀመሪያ የእራስነት ማዕረግ ሲሰጡ ከአባታቸው ታናሽ ወንድም ዳርጌ ሳህለ ሥላሴ ጋር በአንድ ቀን የእራስነት ማዕረግ ሰጧቸው:: ምኒልክ ጎበናን ከመውደዳቸው የተነሳ በገና ሲደረድሩ
ጎበና ጎበና ጎበና የኔ
የጦር ንጉሥ አንተ ያገር ንጉሥ እኔ
እያሉ ያወድሷቸው እንደነበር ይነገራል:: ይሁን እንጂ በእንደዚህ አይነት ፍቅርና መተማመን መካከል ጎበና የምኒልክን አልጋ ተመኙና የመፈንቅለ መንሥት ሴራ ሲያሴሩ ተነቅቶባቸው ተይዘው ዙፋኑን ችሎት ቀረቡ:: ችሎት ላይ የተቀመጡት መኳንንት በየተራ ፍርድ ሰጡ:: ፍርዱም አንዳንዶቹ ሲታመንና ሲወደድ ለከዳሰው ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱባቸው:: አንዳንዶቹ ደግሞ በእርግጥ ሲታመኑ መክዳት ትልቅ ጥፋት ነው ነገር ግን ከዚህ በፊት ብዙ ውለታ የሠሩ ስለሆነ በሞት ሳይሆን በእስራት ይቀጡ ሲሉ ፈረዱ:: የመጨረሻውና የሚጠናው ፍርድ በምኒልክ የሚሰጠው ስለሆነ: እምዬ ምኒልክም እዲህ በማለት ፍርዳቸውን ሰጡ:: 'ጎበናን አሳድጌ ከዚህ ለማድረስ 30 ዓመት ፈጅቶብኛል:: ስለዚህ 30 ዓመት የደከምሁበትን በአንድ ስህተት ገደል አልሰደውም:: ጎበና እንኳን ሞት አይታሰርም ድሮ እንደነበረው ይኖራል ::' ብለው በነፃ ለቀቋቸው::
ይህ አይነት ልበሰፊነትና ምህረት ከሳቸው በሁዋላ ከመጡት መሪዎች አልታየም:: እነ በላይ ዘለቀን በገመድ አንጠልጥለው ሰቅለው ገለዋል:: ደርግንም ያየነው ነው አገሪቷ ስንትና ስንት ገንዘቧን ከስክሳ ያስተማረቻቸውን ጀኔራሎች ያውም ችግር ውስጥ ሁና የእነሱን ሙያ በምትፈልግበት ጊዜ 11ዱን ግሏል:: ከደርግ በሁዋላ የተከሰተውን መንግሥት በሉኝ ባይማ ከመንግሥ ቁጥር አስገብቶ መተቸት ተገቢ ነው ብየ አላምንም::

እምዬ ምኒልክ በሰው ልጆች እኩልነት የሚያምኑ ደግ መሪ ነበሩ:: ለዚህም አንድ ምሳሌ የሚሆነን የጅማው ገዥ አባጅፋር ያካባቢውን ሰዎች ባሪያ እያሉና እየሸጡ ሲያስቸግሯቸው ሰውን ባሪያ ብለው እንዳይሸጡ ከጻፉላቸው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ውስጥ '... አንተ ሰውን ባሪያ እያልኽ መሸጥ ተው እኛ ሁላችንም የሥላሴ ባሪያዎች ነን::....' ይህ ሁላችንም የሥላሴ ባሪያዎች ነን ሲሉ በዓራያ ስላሴ አምሳል የተፈጠረ ሰው አይበላለጥም በሰውነቱ እኩል ነው:: ነው:: ጉልበት ያለው ደካማውን ባሪያ ብሎ ሊሸጠው ሊለውጠው መፈቀድ የለበትም ነው እምነታቸው:: በዚያን ጊዜ አንድ ንጉሰነገሥት እራሱን በትህትና ዝቅ አርጎ ከኅብረተሰብ መደብ ከመጨረሻው ወለል ላይ ከሚገኙት ጉልበታም ባሪያ እያለ ከሚሸጣቸው የማኅበረሰብ ክፍል ጋር አንድ ነን የፈጣሪ ባሪያዎች ነን ያለ ከምኒልክ ሌላ የለም ብል የምሳሳት አይመስለኝም:: ለሚመሩት ሕዝብ ከነበራቸው ትህትናና ርህራሄ የተነሳም ሕዝባቸው ስለወደዳቸው እንደ እናት እምዬ ብሎ የጠራቸውም ምኒልክን ብቻ ነው::
ስለዚህ ይህን የነፃነታችን የማዕዝን ድንጊያ የሆነውን የ123ኛውን የአድዋን ድል ስናከብር ድሉ እውን እንዲሆን በብልሃትና በጀግንነት የመሩትን አጤ ምኒልክንና እቴጌ ጣይቱን እንዲሁም በጦርነቱ የወደቁትን ጀግኖች እንድንዘክራቸው አሳስባለሁ:: በአድዋ ጦርነት የእሴት አያቶቻችን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ማሳሰብ እወዳለሁ:: ያለ እናቶቻችን ተሳትፎ ድሉን መቀዳጀት መቻላችን የማይታሰብ ነው::
ኢትዮጵያ አሁንም እንደ እምዬ ምኒልክ ያለ መሪ ትፈልጋለች::

መልካም የድል መታሰቢያ ቀን ይሁንላችሁ
ዐወቀ አበጋዝ